DMU

Advanced Journal of Interdisciplinary Studies 8(2024) 1470-1483

Journal homepage: www.ajids.com.et

AJIDS

Volume 8(2), Dec 2024

# የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ እና ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ በምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ

ምንታምር ልንገርህ አያሌው

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል፣ማህበራዊ ሳይንስና ሰባዊነት ኮሌጅረ፤ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ደብረ ማርቆስ ፣ ኢትዮጵያ

*Corresponding author email: lmintamir@gmail.com/ lmintamir_lingerih@dmu.edu.et

**አጠቃሎ (Abstract)**

*የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ርዕስ "የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ እና ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ በምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ" የሚል ሲሆን ይህን ጥናት ለማጥናት ያነሳሳኝ ዋና ምክንያት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በተለይም ከማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ አንፃር በተለያዩ ድረ ገፆችና ቤተ መፅሀፍት በተደረገው ዳሰሳ የተጠኑ ጥናቶች ማግኘት ባለመቻሌ ያንን ክፍተት ለማጥበብና የማህበረሰቡን የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ እና ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ ለአካዳሚያዊ ውይይት ማቅረብ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ መግለፅ፣ ማህበረ- ስነልቦናዊ ፋይዳ ተንትኖ ማሳየትና የክዋኔው ትዕምርት መተርጎም ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ ኢትኖግራፊክ የአጠናን ስልት ተከትሎ በክዋኔ፣ በስነልቦና ትንተናና በትዕምርታዊ ንድፈ ሃሳብ የተነተነ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ የመስክ መረጃዎች የተሰበሰቡት በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ከተመረጡ አራት ወረዳዎች (እነማይ፣ ጎዛምን፣ ባሶሊበንና እናርጅና እናውጋ) ነው፡፡ መረጃው ከነዚህ ወረዳዎች በምልከታ፣ አላማ ተኮርና ጠቋሚ (Snowball) የንሞና ዘዴ በመጠቀም ከተመረጡ አስራ አምስት ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች በቃለ መጠይቅና ከአምስት ቡድን ተኮር ውይይት ተሰብስቦ በገላጭ (Descriptive)፣ ተራኪ እና ተርጓሚ (Interpretative) የመረጃ መተንተኛ ዘዴ መረጃው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ የጥናቱ ግኝት የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ በልጃገረዶች ከነሃሴ አስራ ስድስት እስከ መስከረም አንድ እንደሚከወን አመላክቷል፡፡ ማህበረሰቡ ይህን የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል በማክበሩም ከፍተኛ የሆነ ማህበረ ስነልቦናዊ ፋይዳ እንደሚያገኝ እንዲሁም እያንዳንዱ ክዋኔ ሀይማኖታዊና ታሪካዊ ተምሳሌት የያዘ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ከጥናቱ ግኝት በመነሳትም የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የዞኑ ማህበረሰብ የእንግጫ ነቀላን ስርዓተ ክዋኔ እና ማህበረ ባህላዊ ዳራ በሌሎች ማህበረሰቦች ዘንድ እውቅና እንዲያገኝ ቢያደርጉ፡፡ በባህል ጥናት ዙሪያ ትኩረት ሰጥተው የሚመራማሩ አጥኝዎች ለብዙ አንባቢያን እንዲዳረስ እውቅና ባላቸው መጣጥፎች (ጆርናሎች) ላይ በስፋት ቢያሳትሙ የሚሉ የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡*

**ቁልፍ ቃላት:-** *የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል፣ ምስራቅ ጎጃም፣ ኢትዮጵያ (Engcha Ritual, East Gojjam, Ethiopia).*

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ "የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ እና ማህበረ-ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ የተሰራ ሲሆን በውስጡም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ አላማ፣ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ ትንተና ውጤት እና ማብራሪያ እንዲሁም መደምደሚያና የይሁንታ ሀሳብ ተካቷል።

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔ ክብረ በዓል (Ritual) በተሰኘው የሀገረሰባዊ ልማድ ዘርፍ ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ክብረ በዓል የሚለው ቃል የእንግሊዘኛውን "Ritual" የሚገልጽ ነው። "Ritual" የሚለው ቃል ትርጓሜውም ልማድ ወይም የሚቆጠር ነባር ባህል ማለት ነው ሲሉ Dorson (1972) እና Kyriakidis (2007) ገልፀውታል።

Salamone and Frank (2004) ደግሞ ክብረ በዓል (rituals) ወጥ የሆነ ብያኔ የሌለው ከመሆኑ የተነሳ በተለያየ የሙያ ዘርፍ ያሉ ሙሁራን (አንትሮፖሎጅስቶች፣ ሶሾሎጅስቶች፣ ቲዎሎጅስቶች፣ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ፎክሎሪስቶች፣ ወዘተ.) እንደተሰማሩበት የጥናት መስክ በየራሳቸው መንገድ በይነውታል ሲሉ ገልፀውታል።

Sims and Stephens (2005፣ 94-95) በበኩላቸው "ክብረ በዓላት የሚባሉት አንድ ቤተሰብ ወይም ማህበረሰብ የሚፈጽማቸውና የማህበረሰቡን ወይም የቤተሰቡን እምነታዊ ማንነት የሚገለፁ አለማዊም ሆኑ መንፈሳዊ ከበራዎች(Ceremonies)ና ክዋኔዎች (Performances) ናቸው።" ሲሉ ክብረ በዓልን እንዲህ ነው ብሎ ለመበየን ያለውን አስቸጋሪነት አመላክተዋል። ሌሎች የፎክሎር አጥኝዎች ክብረ በዓል የሚያጠኑበትን ምክንያት ሲገልጹ ሀገረሰባዊ ስርዓቶች ከውስብስብነታቸውና ከተውኔታዊ ባህርያቸው የትርጓሜ ጥልቀት የተነሳ የአንድን ማህበረሰብ ወግ፣ ልማድ፣ እምነት፣ እሴትና ማንነት ተጨባጭ አድርጎ የማሳየት አቅማቸው ከፍተኛ ስለሆነ ነው ይላሉ።

Eriksen (2001) እና Rappaport (1992) የአንድ ማህበረሰብ ክብረ በዓል የራሱ ቅርጽ ያለውና የክዋኔ ቅደም ተከተሉ የማይለዋወጥ ለከዋኙ የፈጠራ ነፃነትን የሚነፍግ ለማህበረሰቡ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ማንነቱን ለማስታወስ የሚያገለግል ስርዓተ ክዋኔ ነው ሲሉ። ሰሎሞን (2010፣23) ደግሞ ክብረ በዓል በአብዛኛው የማይቀያየር፣ መደበኛ የድርጊት ቅደም ተከተልና የከዋኞች ፈጠራ የማይታከልበት ቅርፅ ያለው ሲሆን አገልግሎቱን በተመለከተ ደግሞ የራሳቸው ደንብ ያላቸው ማህበረሰባዊ ሁነቶች ሲሆኑ ሰዎች ከፈጣሪያቸው ጋር መንፈሳዊ ግንኙነት የሚፈጥሩባቸው መንገዶች ናቸው ይላቸዋል። Cooke and Macy (2005) ክብረ በዓላት የአንድን ማህበረሰብ ስርዓተ ከበራ ከማሳየት ባለፈ አዲስ ባህል እንዲፈጠር የማድረግ፣ ያለውን የመንከባከብና የማስተዋወቅ ከፍተኛ አስተዋፆ አሏቸው ሲሉ ገልፀውታል።

በአጠቃላይ ከነዚህ ሙሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ክብረ በዓላት የሚባሉት በተለያዩ ሁኔታዎችና ምክንያቶች አንድ ቡድን ወይም ማህበረሰብ በዓለማዊም ሆነ መንፈሳዊ መልኩ የሚፈጽማቸው፣ የማህበረሰቡን እምነት፣ ማንነትና እሴት የሚያንፀባርቁ ከበራዎችን (Ceremonies) የመሰሉ ክዋኔዎች (Performances) መሆናቸውን ነው። የክብረ በዓላት ክዋኔዎችና ከበራዎች የሚፈፀሙበት ሁኔታና ምክንያት እንደየሙሁራኑ ፍልስፍና የትምህርት ዝግጅት የተለያየ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ

ችግርን ለመቋቋም የሚደረጉ ስርዓቶች (Crisis rites)፣ ዓመታዊ ስርዓቶች (Calendrical rites)ና የህይወት ምዕራፍ ስርዓቶች ናቸው (Rites of passage) ሲሉ እነ Sims and Stephens (2005) እና Turner (1969) ገልፀውታል፡፡

Bell (1977) ደግሞ የክበራ አይነቶችን የሽግግር በዓላት፣ ዓመታዊ በዓላት፣ የምስጋና በዓላት፣ የመንፃት በዓላት፣ የአፅዋማትና የደስታ በዓላት እንዲሁም የፖለቲካ በዓላት በማለት በስድስት ከፍለዋቸል፡፡ ዓመታዊ ስርዓቶች (Calendrical rites) የሚባሉት አንድ ማህበረሰብ የራሱን ዘመን አቆጣጠር ተከትሎ በተመሳሳይ ጊዜ በየዓመቱ የሚፈፅማቸው ስርዓቶች ሲሆኑ ማህበረሰቡ በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ ታሪካዊ ወይም ሐይማኖታዊ ድርጊቶችን የሚያስታውስባቸውና ወቅትን ጠብቀው በሚመጡ እንደ ዘር መዝራት፣ የምርት ስብሰባ ወቅትና ለአዲስ ዓመት መቀበያ የሚደረጉ ስርዓቶችን ይመለከታል Bell (1977) እና Salamone (2004)፡፡ Salamone (2004) አያይዘውም ዓመታዊ ክብረ በዓላት የሚከውኑት ስርዓቱን ለመከወን ከተለያየ ቦታ የሚሰበሰቡ የማህበረሰብ አባላት በሚፈጥሩት መስተጋብር ሲሆን እያንዳንዱ የማህበረሰብ አባልም የሚያገኘው አንዳች ፋይዳ እንደሚኖር በማመን ነው ሲሉ ገልፀውታል፡፡

ይህ ጥናትም Bell (1977) ከዘረዘሯቸው የክበረ በዓላት ዓይነቶች መካከል ዓመታዊ በዓላትና የመንፃት በዓላት አጣምሮ የያዘ ነው፡፡ የBell (1977) ሀሳብ የተመረጠበት ምክንያት የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ በምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ውስጥ የሚከበረው ዓመት ጠብቆ ለአዲስ ዓመት መቀበያ እንዲሁም ስርዓተ ክዋኔዎች ከመንፈሳዊና ከአካላዊ ደዌ ለመንፃት የሚፈፀሙ ስለሆኑ ነው ፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ዓመታዊ የሆነውን የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል በማንና እንዴት ያከብረዋል? ማህበረሰቡ ይህን በማክበሩ ምን ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ ያገኛል? ክዋኔውስ ምን ትዕምርታዊ ጉዳይ አለው የሚሉ ሀሳቦችን በመተንተንና በመተርጎም ላይ ያተኩራል፡፡

### 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት እንዳጠና ያነሳሳኝ አንደኛው ምክንያት በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተለያዩ ድረገፆችንና ቤተመፅሀፍትን ስዳስስ ያገኘሁት ጌታቸው እምሬና ሌሎች (2011 ዓ.ም)"*የእንግጫ ነቀላ በዓል ታሪካዊ ዳራ፣ ክዋኔ፣ ፋይዳ፣ ተግዳሮቶችና ምቹ አጋጣሚዎች*" በሚል ያካሄዱት ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም ርዕሱ በዚህ መልኩ ይፃፍ እንጂ ዋና ትኩረቱን ያደረገው የክብረ በዓሉን ታሪካዊ ዳራ ማሳየት፣ በክበረበዓሉ ወቅት የሚደረደሩትን ቃል ግጥሞች መሰብሰብና አሁን ክዋኔው በአለበት አለመቀጠሉን ማሳየት ላይ ብቻ ነው እንጂ የክዋኔውን ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳም ሆነ በክዋኔው ወቅት ያሉ ትዕምርታዊ ጉዳዩችን ባለመዳሰሱ ያንን ክፍተት ለማጥበብ ነው፡፡ ሁለተኛው አነሳሽ ምክንያት በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ በርካታ ዓመታዊ በዓላት የሚከበሩ ሲሆኑ ከሌሎች በዓላት የበለጠ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎበት ሲከበር ያስተዋልሁት ይህንን የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ የማህበረሰቡ መገለጫ የሆነውን የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔ፣ ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ እና የክዋኔው ትዕምርታዊ ጉዳይ በሳይንሳዊ መንገድ አጥንቶ ለአካዳሚያዊ ውይይት ለማቅረብ በማሰቤ ነው፡፡

### 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ እና ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳን መተንተን ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ መግለፅ፤
- የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ ማብራራት፤
- የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓሉ ላይ የሚሳተፉትን አካላትና የሚጠቀሙበትን ቁሶች ትዕምርት መተርጎም ናቸው፡፡

### 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ ከጠቀሜታዎቹ መካከል በዋናነት የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- ✓ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በፎክሎር፣ በሶሻል አንትሮፖሎጅ፣ በታሪክ፣ በባህልና ቅርስ ጥበቃ ዙሪያ ጥናት ለሚሰሩ ተመራማሪዎች የመነሻ ሀሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡
- ✓ ማህበረሰቡ ይህን ክብረ በዓል በማክበሩ የሚያገኘውን ማህበረ ሰነልቦናዊ ፋይዳ በመመርመር በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚዘጋጅ የባህል ፖሊሲ፣ የትምህርት ስርዓትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ግብዓት በመሆን ያገለግላል፡፡
- ✓ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ፣ የከበራውን ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ እና የክዋኔው ትዕምርት በዩኒስኮ ለማስመዝገብ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

### 1.5. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ በዋናነት የሚያተኩረው የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ዓመት ጠብቆ የሚያከብረውን የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ መግለፅ፣ ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ መተንተንና የክዋኔውን ትዕምርት ተርጉሞ ማሳየት ላይ ነው፡፡ ርዕሰ ጉዳዩ እዚህ ላይ ያተኮረው ከተጠኚው ማህበረሰብ ጋር ረጅም ጊዜ አብሬ ስኖር ከሌሎች በማህበረሰቡ ዓመት ጠብቀው ከሚከውኑት ክብረ በዓላት ይልቅ የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔ በድምቀትና በተደጋጋሚ ሲከበር በማየቴ ያለውን ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ ለመመርመር ካለኝ ጉጉት ነው፡፡ ከቦታ አንፃር ምስራቅ ጎጃም የተመረጠው የተጠኚውን ማህበረሰብ ባህልና ወግ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ ለረጅም ጊዜ አብሬ ስኖር በአግባቡ ስለተረዳሁ በመረጃ ስብሰባ ወቅት የማህበራዊ ተግባቦት ችግር እንደማይገጥመኝ እርግጠኛ ስለሆንሁ ነው፡፡

### 1.6. የንድፈ-ሃሳብ ማዕቀፍ (Theoretical Framework)

የዚህን ጥናት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑት ክዋኔያዊ ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔው፣ የማህበረ-ስነልቦና ትንተና ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ በእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔ የሚሳተፉና የሚታደሙ አባላት ከክዋኔው የሚያገኙትን ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ፤ እንዲሁም ትዕምርታዊ ንድፈ ሃሳብን መሰረት በማድረግ በእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔው ወቅት የሚሳተፉ የማህበረሰቡ አባላት እና በክዋኔው ወቅት የሚጠቀሙባቸው ቁሶች ያላቸው ትዕምርታዊ ጉዳይ ነው፡፡

## 2. የምርምር ዘዴዎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የጥናቱ ዓይነት፣ የቦታ አመራረጥ፣ ንሞና እና ናሙና፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ አቀራረብና ትንተና፤ ሥነ-ምግባራዊ ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1. የጥናቱ ዲዛይን

ይህ ጥናት ኢትኖግራፊክ የአጠናን ስልትን የተከተለ ነው። የአጠናን ስልቱ ይህ የሆነበት ምክንያት የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔ ወቅት ተሳታፊና ታዛቢ ተመልካች ሁኜ ከነሃሴ አስራ ስድስት ሁለት ሺ አስራ አራት እስከ መሰከረም አንድ ሁለት ሺ አስራ አምስት ዓመተ ምህረት ድረስ መረጃ ለመሰብሰብ አብሬ መቆየቴ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ይህን የአጠናን ስልት መጠቀም ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ጥናቱ የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብን የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ከበራ፣ የከበራውን ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ ተንትኖ በማሳየትና የክዋኔውን ትዕምርት በመተርጎም ላይ ስለሚያተኩር ነው። እንደ Simes and Stepens (2005) መረጃ፤ ማህበራዊ ከበራ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ምርምሮች ኢትኖግራፊክ የአጠናን ስልትን መከተልና መተግበር እንዳለባቸው ይመክራሉ።

### 2.2. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት አላማ ተኮር የንሞና ዘዴን በመጠቀም በምስራቅ ጎጃም ዞን ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አራት ወረዳዎች (እነማይ፣ ጎዛምን፣ እናርጅና እናውጋ እና ባሶ ሊበን) ተመርጠዋል። እነዚህ ወረዳዎች የተመረጡበት ምክንያት የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ከሌሎች ወረዳዎች ይልቅ በድምቀት የሚከወንባቸው (የሚከበርባቸው) መሆናቸውን ከማህበረሰቡ ጋር አብሬ በኖርሁባቸው አመታት በማረጋገጤ ነው። ይህ መሆኑ ደግሞ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይገኛል ተብሎ ስለታሰበ ነው። ስለዚህ የጥናቱ ተተኳሪም እነዚህ ወረዳዎች ብቻ ናቸው።

### 2.3. ንሞና እና ናሙና

የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በአላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ከተመረጡት አራት ወረዳዎች ነው። በእነዚህ ወረዳዎች የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ከነሀሴ 16/12/2014ዓ.ም-01/01/2015 ዓ.ም ከሚከውኗቸው የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔዎች መካከል አላማ ተኮር የንሞና ስልትን በመጠቀም የእንግጫ ነቀላ የሚጀመርበት ነሃሴ አስራ ስድስት፣ ጳጉሜ ሙሉ አምስቱን ቀናትና መስከረም አንድ ቀን በምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል። አላማ ተኮርና ጠቋሚ (Snowball) የንሞና ዘዴን በመጠቀም ደግሞ ከተመረጡ አስራ አምስት ቁልፍ መረጃ አቀባይ ሰዎች ማህበረሰቡ ይህን ክብረ በዓል በማክበሩ የሚያገኘውን ማህበረ ስነልቦናዊ ፋይዳና የክዋኔውን ትዕምርት የሚመለከቱ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ ተሰብሰብዋል። ግልጽነት በሌላቸው እና አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የወል ስምምነት እንዲኖር ለማድረግ ከላይ በቁልፍ መረጃ ሰጭነት የተሳተፉ አስራ አምስት ሰዎችና በአላማ ተኮር የተመረጡ ሃያ አምስት በድምሩ አርባ መረጃ ሰጪዎች የተሳተፉበት አምስት ቡድን ተኮር ውይይት ተካሂዷል። በእያንዳንዱ የቡድን ተኮር ውይይት ቁጥራቸው ከአምስት እስከ ስምንት የሚደርሱ ሰዎች በአመች የንሞና ዘዴ በተመረጠ ቦታ ላይ ተሳትፈዋል። በእያንዳንዱ የቡድን ተኮር ውይይት ላይም የማህበረሰቡን የእንግጫ ነቀላ ስርዓት የሚያውቁ የተጠኘው ማህበረሰብ የእድሜ ባለፀጋ ሴቶችና ወንዶች እንዲሁም የክብረ በዓሉ ተሳታፊ ወጣት ወንዶችና ሴት ተሳትፈውበታል።

### 2.4. የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ነው። በምልከታ የማህበረሰቡ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ በማን፣ ከመቼ እስከ መቼና

እንዴት እንደሚከወን፣ በቃለ መጠይቅ ደግሞ ማህበረሰቡ ይህን ክብረ በዓል በማክበሩ የሚያገኘውን ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳና የክብረ በዓሉ ስርዓተ ክዋኔ ትዕምርት የሚመለከቱ መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን የቡድን ተኮር ውይይት በመጠቀም ደግሞ በሁለቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሲሰበሰቡ እርስ በእርስ የተጣረሱ ወይም አከራካሪ እይታዎችን ወደ አንድ ድምዳሜ ላይ ለማድረስ የሚያግዙ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

### 2.5. የመረጃ አቀራረብ እና ትንተና

ይህ ጥናት የቀረበው ገላጭ (Descriptive)፣ ተራኪ እና ተርጓሚ (Interpretative) በሆነ መንገድ ነው፡፡ ምክንያቱም የተሠበሠበውን መረጃ መግለፅ፣ መተረክና መተርጎም ለዚህ ጥናት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን አቀራረብ በመጠቀም የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔና ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ በመግለፅና በመተንተን እንዲሁም የክዋኔውን ተሳታፊዎችና በክዋኔው ወቅት የሚጠቀሙባቸውን ቁሶች ትዕምርታዊ ጉዳይ በመተርጎም ቀርቧል፡፡

### 2.6. ሥነ-ምግባራዊ ጉዳዮች

በምርምር ስራ ወቅት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገቡ ስነምግባራዊ ጉዳዮች በርካታ ሲሆኑ እንደ McLeod and Rachel Thomson(2010) አገላለፅ የአንድን ጥናት አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የሚሰጡ መረጃ አቀባዮችን በመጀመሪያ የጥናቱን ጉዳይ በተገቢው መንገድ አስረድቶ መረጃ ለመስጠት ሙሉ ፍቃደኝነታቸውን ማግኘት እና በነፃነት መረጃ መስጠት እንዲችሉ ማድረግ አንዱ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱን ለማካሄድ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት የትብብር ደብዳቤ ከማፃፍ ጀምሮ ከመረጃ ሰጭ አካላት ጋር ስለምርምሩ ምንነትና ዓላማ ውይይት በማድረግ በምርምር ስራው በቅንነት እንዲሳተፉና መረጃ የመስጠት ሂደቱም በፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህ ጊዜ ለምርምሩ የሚሰጡት መረጃ ከጥናቱ ዓላማ ውጭ እንደማይውልና የመረጃ ሰጭዎች ማንነትም ለማንም እንደማይገለፅ ተነግሯቸዋል፡፡

## 3. የመረጃ ትንተና ውጤት

በዚህ ክፍል የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ ተገልፆ፣ ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳው ተተንትኖና በክዋኔው ወቅት የሚሳተፉ አካላት እና የሚጠቀሙባችው ቁሶች ትዕምርት ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

### 3.1. የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ

የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ዓመት ጠብቆ ከሚያከብራቸው ዓመታዊ በዓላት መካከል አንዱ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ነው፡፡ ይህ ክብረ በዓል የአሮጌው አመት ማብቂያ የአዲሱ ዓመት መግቢያን ለማብሰር የሚከበር በዓል ሲሆን በዓሉን በማክበር በዋናነት የሚሳተፉት ወጣት ወንዶችና ሴቶች ናቸው፡፡ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔም ከነሃሴ አስራ ስድስት እስከ መስከረም አንድ ድረስ የሚከበር ሲሆን እንግጫ የሚባለው የሳር ዓይነት ቅጠሉ ከሌሎች ሳሮች አንፃራዊ ጠቆር ያለ አረንጓዴ ከለር ያለው ነው፡፡ ይህ የሳር ዓይነት በማህበረሰቡ ዘንድ እንግጫ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ይህን ሳር በመንቀል በመጎንጎንና አዲስ ዓመት መምጣትን በማብሰር የሚሳተፉትም በዋናነት ልጃገረዶች ናቸው፡፡ በምልከታዬ ወቅት (ቢቸና ደብር፣16/12/2014ዓም) እንዳስተዋልሁት ልጃገረዶቹ የመደላደል

ቀን[1] ወይም ነሃሴ አስራ ስድስት እንግጫ ነቅለው "አበባ አየሁሽ ለምለም" እያሉ እያዜሙ ሜዳ ላይ ይጫወታሉ፡፡ ወንድ ጎረምሶች ዙሪያቸውን ያጅቧቸዋል፡፡ አንዱ ወንድ አንዷን ልጃገረድ (ሴት ልጅ) ጉንጯን ይስማል፡፡ ይህን ለምን እንደሚያደርጉ በቃለ መጠይቁ ወቅት ወይዘሮ ያለምወርቅ ሞሱ፣ (ስርእየሱስ፣ 17/12/2014ዓ.ም) እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል፡፡ "እንዳየሻቸው እንግጫውን እየነቀሉ ከሚጫወቱት ልጃገረዶች መካከል ጎረምሶች ልባቸው የከጀላትን መርጠው ጉንጭ የሚስሙት የከንፈር ወዳጅ እንድትሆናቸው ነው፡፡ በዛሬ ቀን ደግሞ ልጃገረዶችን ለምን ተሳማችሁ ጎረምሶችንም ለምን ሳማችሁ ብሎ የሚቆጣ ቤተሰብ የለም ዛሬ እንደልባቸው ነው የሚጫወቱት…፡፡" ልጃገረዶችም ከነሀሴ አስራ ስድስት ቀን ጀምሮ እስከ እንቁጣጣሽ ወይም አዲሱ ዓመት መግቢያ መስከረም አንድ ድረስ የተለያዩ ዝግጅቶችን ሲያደርጉ በምልከታ በቆየሁባቸው (16-30/12/2014 ዓ.ም) ቀናት አስተውያለሁ፡፡ ከሚያደርጓቸው ዝግጅቶች መካከል ከነሃሴ አስራ ስድስት የመደላድል ቀን ጀምሮ እስከ ነሃሴ 22 ድረስ ልጃገረዶች ከስራ ነፃ ሆነው[2] እንግጫ፣ አደይ ወይም እንቁጣጣሽ አበባ ያለበትን ቦታ እያሰሱ እነዚያን አበቦችና እንግጫዎች እነሱ ሊነቅሉትና ሊቆርጡት እንደሚችሉ ለጓደኞቻቸው እያሳዩ ሲጫወቱ በምልከታዬ ወቅት አስተውያለሁ፡፡

ከነሃሴ ሃያ ሶስት እስከ ሰላሳ ድረ*ሥ* የስራ ወቅት ስለሆነ በየማሳው አረም በሚያርሙ ሰዓት የትኛው ማሳ ላይ እንግጫ እንዳለ ከስራቸው ጎን ለጎን ይለያሉ፡፡ ከጳጉሜ አንድ እስከ አምስት ወይም ስድስት ደግሞ ልጃገረዶች አንድ ላይ ተሰባስበው በየቤቱ በተራ በማደር ጎህ ሲቀድ ወይም ዶሮ ሲጮህ እየጨፈሩ ወንዝ እየሄዱ ወፍ ባልቀመሰው ውሃ[3] ይታጠቡና እየጨፈሩ ይመለሳሉ፡፡ ቀን ቀን ወላጆቻቸውን በስራ እያገዙ ያልዘረዘረ (አበባ ያላወጣ) እንግጫ እየመረጡ ይነቅላሉ፡፡ ጳጉሜ አምስት[4] ወይም ስድስት የተነቀለውን እንግጫ ከሰፈር ወጣት ወንዶች ጋር በመሆን እንቁጣጣሽ አበባውን ጨምረው በሶስት ድርብ ይጎነጉኑታል፡፡ ወንዶቹ በዚያን ጊዜ ችቦ ለኩሰው እንግጫ ለሚጎነጉኑ ልጃገረዶች ያበሩላቸዋል (ይርጋለም ታምሬ፣ኮርክ፣23/12/20 ዓ.ም)፡፡

ልጃገረዶች መስከረም አንድ ወይም የቅዱስ ዮሀንስ እለት አዲስ ልብሳቸውን ለብሰው ጳጉሜ አምስት ወይም ስድስት ማታ ላይ የጎነጎኑትን እንግጫ በአንገታቸው ላይ አድርገውና በራሳቸው ላይ አስረው በየቤቱ እየዞሩ አበባ አየሁሽ ለምለም የሚል ዜማ እያዜሙ በቤቱ ውስጥ ባሉ ምሰሶዎች፣ በቡሀቃ (በሊጥ ማቡኪያው) አንገት ላይ ሌማቱ ክዳን መያዣ ላይ እያሰሩ የሰፈሩን ቤቶች በሙሉ ካደረሱ በኋላ ወደ ቤተክርስትያን በመሄድ ቤተክርስትያኑን ሶስት ጊዜ ዞረው የቀረውን እንግጫ ጉንጉን

[1] የመደላደል ቀን ማለት በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ከነ ሀሴ አስራ ሶስት ጀምሮ ክረምቱ እየ ወጣ ነው "በዚ ከዋለ የለምክረምት ዶሮ ከጮኸ የለም ለሊት" ተብሎ ይታሰባል፡ ፡ ወጣት ሴቶችና ወንዶችም ነ ሀሴ አስራ ስድስት ወጥው በነፃነት የሚጫወቱበት የክረምቱ ዝናብና ጭቃ ሜዳውም ላይ ያለው ጭቃ የሚቀንስበት የከንፈር ወዳጅ የሚያበጁበትና የወደፊት ህይወታቸውን የሚደላደሉበት ተብሎ ስለሚታሰብ ያንን ቀን የመደላደል ብለው ይጠሩታል፡ ፡

[2] በእነዚ ቀናት ከስራ ነፃ የሚሆኑት የጥናት አካላይ ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ስለሆነ በእነዚህ ቀናት ደግሞ የሚያምበዓል ስለሆነ ስራ አይሰራም፡ ፡

[3] ወፍ ያልቀመሰው ውሃ ማለት ከምንጩም ሳይቀዳለት በጥዋት ከሚደረዋ የ ወጣች ወፍ እንኳን ያልጠጣችለት ማለት ነ ው፡ ፡

[4] ጳጉሜ አምስት ወይም ስድስት የ ተባለበት ምክንያት አስራ ሶስተኛው ወር ከአራት አመት አንዴ ስድስት ስለምትሆን ያንን ለመጠቆም ታስቦ ነ ው፡

በሙሉ ቤተ ክርስትያን ምሰሶዎች ላይ ሲያስሩ በምልከታው ወቅት (የጥጃን ቀበሌ፣ 01/01/2015ዓ.ም) አስተውያለሁ፡፡ ይህን ለምን ታደርጋላችሁ ብየ ባደረግሁላቸው ቃለመጠይቅ መሰረት የእንግጫ ነቀላ ተሳታፊዋ እናት ወይዘሮ ባዩሽ (የጥጃን ቀበሌ፣01/01/2015 ዓ.ም) እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል፡፡

> *…ከነሃሴ አስራ ስድስት ጀምሮ ልጃገረዶችና ጎረምሶች እንደፈለጋቸው ነው የሚጫወቱት ዛሬም እንዳየሻቸው የአዲሱ ዓመት መምጣት በየቤቱ እየዞሩ ሲያበስሩና በእኛ እምነት (በኦርቶዶክስ ክርስትያን) ማንም ዞሮዞሮ ከቤተ ክርስትያን አይቀርም ማሳረጊያው ቤተክርስትያን ነው ብለው ነው መጨረሻ ላይ እዚያ የሄዱት ዙሮ ዙሮ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከሞት ይባል የለ መጨረሻም ስንሞት እዚያ ነው የምንሄደው …፡፡*

### 3.2. የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል መከበሩ ለማህበረሰቡ ያለው ማህበረ-ስነልቦናዊ ፋይዳ

የምስራቅ ጎጃም የማህበረሰብ አባላት የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓልን ዓመት ጠብቀው የሚያከብሩት የራሳቸውን ልማድ፣ እምነት፣ እሴት፣ ማንነት፣ ማህበራዊ ትስስር በጠበቀ እና የማህበረሰቡን ስነልቦና በገነባ መልኩ ነው፡፡ ምክንያቱም የቡድን ተኮር ውይይት አንድ ተወያዮች (የጁቤ ከተማ፣ ጳጉሜ 5/2014 ዓ.ም) እና የቡድን ተኮር ውይይት ሁለት (ጎዛምን ወረዳ ፅ/ቤት አካባቢ፣ ጳጉሜ 04/2014 ዓ.ም) ተወያዮች እንደገለፁት በመደላደሉ ቀን የወጣቶች የከንፈር ወዳጅ ማበጀት በሶስት መልኩ ለማህበረሰቡ ስነልቦናዊ ፋይዳን ይሰጣል፡፡ አንደኛ ልጃገረዶች በጎረምሶች ዘንድ ተወዳጅ መሆናቸውን የሚያውቁበት ጊዜ ስለሆነ ስነልቦናዊ እርካታን ያገኛሉ፡፡ ሁለተኛው መደላደል የተባለበት ምክንያት የከንፈር ወዳጅ የሌለው የከንፈር ወዳጅ አበጅቶ ውስጡን የሚያረጋጋበት ወይም የሚደላደልበት የስሜት መረጋጋት የሚፈጠርበት፤ የትዳር አቻ ያገኙ ያህል የመንፈስ እርካታ ያገኛሉ፡፡ ሶስተኛው በሴት ወላጆች ዘንድ በተለያየ መልኩ ልጄ ተፈላጊ ናት ኮትኩቼ ነው ያሳደግኋት በማለት የወላጅነት ግዴታ የተወጡ መሆናቸው ስለሚሰማቸው ከፍተኛ ቤተሰባዊ እርካታን ይፈጥራል፡፡

ጳጉሜን በሙሉ በወንዝ መታጠባቸው ደግሞ ከአካላዊና ከመንፈሳዊ መንፃት ጋር ስለሚያይዙት አዲሱን ዓመት በአዲስ መንፈስ በሙሉ ጤና ተቀብየዋለሁ የሚል ስነልቦናዊ እርካታን ያገኛሉ፡፡ ምክንያቱም የጳጉሜ ውሃ በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ ፀበል እንደሚቆጠርና ከአካላዊም ሆነ ከመንፋሳዊ ህመም ይፈወሳል ተብሎ እንደሚታሰብ መረጃ ሰጭዬ አቶ አበበ (ተንጉማ፣ ጳጉሜ 02/2014 ዓ.ም) ገልፀውልኛል፡፡ ወ/ሮ ዓለምገናም (ገደብ፣ ነሃሴ 17/12/2014 ዓ.ም) ይህንን ሃሳብ እንዲህ ሲሉ አጠናክረውልኛል፡፡ “ቋ[ጳ]ጉሜን በሙሉ ልጆቹ ወንዝ እየሄዱ በእድሜ ከፍ ከፍ ያሉት (ከአስራ ስምንት አመት በላይ) ደግሞ ፀበል ቦታ እየሄዱ የሚጠመቁት ወንዙ በሙሉ በቋ[ጳ]ጉሜ ፀበል ነው ምክያቱም በቋ[ጳ]ጉሜ ሰማይ ይከፈታል የሚወርደው ዝናብ በሙሉ ፀበል ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ” በዚያ የታጠበ ደግሞ ከአካላዊም ሆነ ከመንፈሳዊ ደዌው (በሽታው) ይድናል፡፡

ስለዚህ አዲሱን ዓመት በንፅህና ተቀብየዋለሁ የሚል መንፈሳዊና ስሜታዊ (ስነልቦናዊ) እርካታን ያገኛሉ፡፡

ጎረምሳ ወንዶች እና ልጃገረዶቹ በተራ በየቤቱ ማደራቸውና ጎህ ሲቀድ ወንዝ ወርደው ታጠበው ወይም ተጠምቀው በሰላም መመለሳቸው ማህበራዊ ሰላምንና ደህንነትን ማረጋገጫ ናቸው፡፡ እንዲሁም የተጎነጎነው እንግጫ መስከረም አንድ ልጃገረዶች የሊጥ ማቡኪያው እና ሞሰቡ ላይ ማሰራቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የበረከት ተምሳሌት ተደርጎ ስለሚወሰድ ከፍተኛ በረከት አገኛለሁ በሚል እምነት ስነልቦናቸው ይደላደላል፡፡ መስከረም አንድ ከራስና ምሰሶው ላይ ታስሮ የነበረው ጉንጉን እንግጫ መስከረም አስራ ሰባት መቃጠሉ ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ በቤቱ ውስጥ የነበረው አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ በሽታ እንደተቃጠለ ተደርጎ ስለሚታሰብ ስነልቦናዊ እርካታን ያገኙበታል፡

### 3.3. በእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓሉ ጊዜ የሚከወኑ ክዋኔዎች ትዕምርት

ከላይ 3.1 የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ስር የተገልፁት የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔዎች በማህበረሰቡ ዘንድ የተለያዩ ትዕምርታዊ ጉዳዮችን የያዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የመጀመሪያው የመደላደል ቀን ተብሎ ነሃሴ አስራ ስድስት የሚከናወነው ስርዓተ ክዋኔ ነው፡፡ ይህ ስርዓት ሶስት ትዕምርት አለው አንደኛው ለማህበረሰቡ የክረምቱ መውጣት መንገሪያ የፀደዩን መምጣት ማብሰሪያ ነው፡፡ መሬቱም መረጋጋቱን መንገሪያ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብም ወይዘሮ እንደገና ሞላ (የጥጃን ቀበሌ፣01/01/2015 ዓ.ም) በቃለ መጠይቁ ወቅት እንዲህ ሲሉ ገለፀውልኛል፡፡ "ነሀሴ አስራ ስድስት የመደላድል ቀን ተብሎ የተሰየመው አንደኛ በክረምቱ መግባት ምድሩም ሰማዩም አልተረጋጋም አሁን መሬቱም ተደላድሏል፤ ክረምቱም ወጥቷል የሚለውን ለማብሰር ነው፡፡ ሲተርቱ ቡሄ ከዋለ የለም ክረምት ዶሮ ከጮኸ የለም ለሊት ይሉ የለ ልጃገርዶችም ይህንን ለማብሰር ነው፡፡"

እንግጫ የሚነቅሉት ልጃገረዶች ያልዘረዘር እንግጫ መንቀላቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የድንግልና ተምሳሌት ሲሆን ድንግልና ደግሞ ከሃጢያት መንፃት ጋር ይያያዛል፡፡ ልጃገረዶች መስከረም አንድ በእንቁጣጣሽ አበባ ያሸበረቀ የእንግጫ ጉንጉን በየቤቱና በቤተክርስትያኑ እየዞሩ የሚያስሩበት ምክንያት አዲስ ዓመት መምጣትን ማብሰሪያ ሲሆን የክዋኔው ተሳታፊዎች ትዕምርትም ከኦርቶዶክስ ክርስትና አስተምሮ ጋር እንደሚሄድ ወይዘሮ ስለእናት (ዘምቦል፣ 18/12/2014 ዓ.ም) በቃለ መጠይቁ ወቅት

> … *አባቶች እንደሚያጫውቱኝ ልጃገረዶቹ እርግቧ ናቸው፡፡ እንግጫው እርግቧ ይዛው የመጣችው ሳር ነው፡፡ ምክንያቱም በጥፋት ውሃ ጊዜ ኖህ ውሃው መጉደሉ እንዲያረጋግጡ መጀመሪያ ቁራን ላከው እሱም በዚያው የሞተውን ሲበላ ቀረ ቀጥሎም እርግቧን ላከ እሱ ውሃው መጉደሉን እይታ ማረጋገጫም ከመሬቱ ላይ ሳር ነቅላ ሄደች፡፡ ኖህም ይህን ባየ ጊዜ ደስ አለው እኛም ልጆች እንግጫ ይዘው ሲመጡ ደስ የሚለን የክረምቱን ማለፍ የፀደዩን መምጣት ማብሰራቸውን ስለምንረዳ ነው" በማለት አብራርተዋል፡፡*

እነጌታቸውም (2011) በጥናታቸው የሃይማኖት አባቶችን ዋቢ በማድረግ ይህንን ሀሳብ እንዲህ ሲሉ አጠናክረውታል፡፡

> *የኖህን ዘመን ሲያስቀምጥ፤ በኖህ ዘመን ሰዎች ሀይማኖታቸውን የረሱበትና ብዙ ሀጢያት የሰሩበት ርኩሰት በምድር ላይ የሞላበት ዘመን ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት እግዚአብሄር ወደ ምድር አስተማሪ ቢልክም ሰዎች ስላልሰሙት በንፍር ሊያጠፋቸው ስለፈለገ ኖህ ደግሞ መልካም ሰው በመሆኑ ከጥፋት እንዲወጣም መረከብ ስራ ብሎ አዘዘው፤ እንዴትም እንደሚሰራ አሳየው፡፡ ከዚያም ኖህም መረከቡን ክፍል ክፍል ሰርቶ ከሚበሉና ከማይበሉ እንስሳት 7፤7 አደርጎ ወደ መረከቡ አስገባ፤ ከዚያም የሰማይም መሰኮት ተከፍቶ መሬትን በንፈር ውሀ አጠፋት፤ ከኖህ መረከብ በስተቀር ምደር በሙሉ ጠፋ ከተወሰነ ጊዜ በኋላም ዓለም ንፈር ዉሃው ሲያቆም ኖህ የመሬትን ደህንነት ለማወቅ ቁራን ላከ፤ እርሱም አዛዉ የሞተውን አየበላ ቀር፤ በሁለተኛ ጊዜም እርግብን ላከ እሷም ለምለም ሳር ይዛ ተመለሰች፡፡ በመሆኑም ለምለም ሳር/ እንግጫ የጥፋት ውሃ መጉደሉን የሚያበስር ነበር፡፡ ኖህም በጣም ደስ አለው፤ምድርም ስላም መሆኑን አረጋገጠ፡፡ በመሆኑም የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል የዚያ ምሳሌ አድርጎ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ክብረ በዓል ነው፡፡*

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ቤተክርስትያኗ የኖህ መርከብ ተምሳሌት መሆኗን ነው፡፡ ምክንያቱም እርግቧ መጀመሪያ ውሃው አለምጉደሉን ለማብሰር ወይራ ቅጠል ቆርጣ ይዛ የሄደችው ኖህ ወደ ሰራት መርከብ ነበር፡፡ ሁለተኛ ውሃው መጉደሉን ለማብሰር ቂጤማ ወይም ለምለም ሳር ቆርጣ የሄደችው ወደ ኖህ መርከብ ነበር፡፡ ልጃገረዶችም እንግጫውን ይዘው ወደ ቤተክርስትያን የሚሄዱት ያንን ታሪክ ለማዘከር ነው፡፡

በቡሃቃው (በሊጡ ማቡኪያ ዕቃ) እና በሞሰቡ ላይ የሚያስሩት ደግሞ የተቦካው ሊጥም እንዲሁም በሞሰቡ ውስጥ ያለው ዳቦ ወይም እንጀራ ቶሎ ቶሎ እንዳያልቅ ወይም እንዲበረክት መልካም ምኞትን ለመግለፅ ነው፡፡ በቤቱ ምሰሶና በልጃገረዶች ራስ ላይ የታሰረው የተጎነጎነ እንግጫ ተቀምጦ ቆይቶ የመስቀል ከደመራው ጋር አብሮ መቃጠሉ ደግሞ በአሮጌው ዓመት በቤቱ ውስጥ የነበረው አካላዊና መንፈሳዊ ደዌ እንደዚህ ተቃጥሏል አዲሱን ዓመት በንፅህና ተቀብለና ማለት ነው ሲሉ ስለእናት (ዘምቦል፣ 18/12/2014 ዓ.ም) በቃለ መጠይቁ ወቅት ገልፀውልኛል፡፡

የእንቁጣጣሽ አበባው ትፅምርት ደግሞ ከንግስተ ሳባ (ማክዳ) ጋር ይያያዛል፡፡ “ንግስት ማክዳ ወደ ሰሎሞን ሄዳ ምኒሊክን ፀንሳ በመስከረም ስትመጣ ሰሎሞን ለማክዳ እንቁ ለጣትሽ ብሎ ሰጥቷታል፡፡ ያንን ይዛ ኢትዮጵያ ስትመጣ የመጣ እንደሆነ በአፈታሪክ ይነግራል" ሲሉ አቶ መላኩ (የጥጃን ቀበሌ፣01/01/2015 ዓ.ም) በቃለ መጠይቁ ወቅት ገልጸውልኛል፡፡ እንዲሁም የእንግጫው ለሶስት መጎንጎን ውክልናን መጋቢ ሞላ (ደብረ ፅሞና፣ 21/01/2014 ዓ.ም) እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል “እንግጫው ለሶስት መጎንጎኑ እኛ እርስ በእርስ በሰንበቴውም በፅዋ ማህበሩም በፍቅር መተሳሰርን የሚያመለክት ሲሆን በእኛ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ዘንድ ደግሞ

የስላሴ አንድነትና ሶስትነት የሚያጠይቅ ነው፡፡” ከመረጃ ሰጪዎች ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔና የክዋኔ ተሳታፊ እንዲሁም የሚጠቀሙበት ቁስ ትዕምርት ከማህበረሰቡ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ዳራ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መሆኑን ነው፡፡

## 4. የጥናቱ ማብራሪያ

በዚህ ክፍል ውስጥ የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች የሚተነተኑ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተገናኘ በሌሎች ጥናቶች ላይ የሚገኙ ቁልፍ የጥናት ውጤቶች እንደየአስፈላጊነታቸው ጥናቱን በሚያጠናክር መልኩ ተዳሰዋል፡፡ የዚህ ጥናት መሰረታዊ ሀሳብ የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ የእንግጫ ነቀላ ክበረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ መግለፅ፣ ማህበረ-ስነልቦና ፋይዳ ተንትኖ ማሳየትና የክዋኔውን ትዕምርት መተርጎም ሲሆን በስሩም 1) የማህበረሰቡን የእንግጫ ነቀላ ክበረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ መግለፅ፤ 2) የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል መከበሩ ለማህበረሰቡ ያለውን ማህበረ- ስነልቦናዊ ፋይዳ መመርመር 3) የክብረ በዓሉ ክዋኔ ተሳታፊዎች እና የሚጠቀሙባቸው ቁሶች ትዕምርት መተርጎም የሚሉ ዝርዝር አላማዎች አሉት፡

የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለከተው የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓልን ዓመት ጠብቀው በአብዛኛው የሚያከብሩት ልጃገረዶች ከነሀሴ አስራ ስድስት እስከ መስከረም አንድ ድረስ ሲሆን ይህ ክብረ በዓል በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከበረውም አሮጌው ዓመት ማለፉንና አዲስ ዓመት መምጣቱን ለማብሰር ነው፡፡ ይህ ግኝትም Bell (1977) የአንድ ማህበረሰብ ክብረ በዓል የሚከበረው አሮጌው ዓመት ማለቁን አዲሱ ዓመት መምጣቱ ለማብሰር ነው በማለት ከገለፁት ፅንሰ ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው የጥናት ግኝት የሚያመለክተው ይህን ክብረ በዓል ማህበረሰቡ በማክበሩ ከአካላዊና መንፈሳዊ ደዌ ወይም ሀጢያ የመንፃት፣ የስሜት መረጋጋትና ማህበራዊ ትስስርን የመጨመር ከፍተኛ የሆነ ማህበረ ስነልቦናዊ ፋይዳዎችን ያስገኝለታል፡፡ ይህ ግኝትም Salmon(2004) ዓመታዊ ስርዓቶች የሚከውኑት ስርዓቱን ለመከወን ከተለያየ ቦታ የሚሰባሰቡ የማህበረሰብ ክፍሎች በሚፈጥሩት መስተጋብር እያንዳንዳቸው የሚያገኙት አንዳች ፋይዳ እንደሚኖር በማመን ነው ሲሉ ከገለፁት ሀሳብ ጋር ይቀራረባል፡፡

ሶስተኛው የጥናት ግኝት የሚያሳየው በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከወኑ የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ከዋኔን የሚከውኑ ልጃገረዶች የኖህ እርግቧ ተምሳሌት በመሆን፣ እንግጫው የጥፋት ውሃው መጉደል የመጣውን እርጥብ ሳር በመወከል፣ ያልዘረዘረ መሆኑ ከንፅህና ወይም ከድንግልና ጋር መያያዙና ቤተክርስትያን ደግሞ የኖህ መርከብ ተምሳሌት መሆኗ፣ አበባው ደግሞ ጠቢቡ ሰሎሞን ለማክዳ (ለንግስተ ሳባ) ለአዲስ ዓመት የሰጣትን ስጦታ የሚወክል ሲሆን በአጠቃላይ የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ ትዕምርት በአንድ ወቅት ከባህሉ ባለቤት እምነትና ታሪክ ጋር ለተፈፀሙ ሀይማኖታዊና ታሪካዊ ክስተቶችን የቆሙ ናቸው፡፡ ይህ ግኝትም Bell (1977) ዓመታዊ ስርዓቶች (Calendrical rites) የሚባሉት አንድ ማህበረሰብ የራሱን የዘመን አቆጣጠር ተከትሎ በተመሳሳይ ጊዜ በየዓመቱ የሚከውናቸው ስርዓቶች ሲሆኑ ማህበረሰቡ በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ ታሪካዊ ወይም ሃይማኖታዊ ድርጊቶችን

የሚያስታውስባቸውና ወቅትን ጠብቀው ከሚመጡ ክብረ በዓላት ጋር ከፍተኛ ትስስር እንዳለው ያመለክታል፡፡

## 5. መደምደሚያና የይሁንታ ሀሳብ

### 5.1. መደምደሚያ

ይህ ጥናት የተከናወነው ሶስት ዋና ዋና ንዑስ አላማዎችን ከግብ ለማድረስ ነው፡፡ የመጀመሪያው የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ መግለፅ፣ ሁለተኛው የክዋኔው ማህበረ ስነልቦዊ ፋይዳ መተንተን ሲሆን ሶስተኛው የክዋኔው ተሳታፊዎችና በክዋኔው ወቅት የሚጠቀሙባቸውን ቁሶች ትዕምርት መተርጎም የሚሉት ናቸው፡፡ ናሙና የተወሰደባቸው ወረዳ ማህበረሰቦች ከነሃሴ አስራ ስድስት ጀምሮ እስከ መስከረም አንድ የሚደርስ ወይም እስከ ቅዱስ ዮሐንስ የሚደርስ የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ከዋኔ ያላቸው ሲሆን እነሱ ነሀሴ አስራ ስድስት የመደላደል ቀን ተብሎ የሚጠራው ሜዳ ላይ የሚደረገው የእንግጫ ነቀላ ጨዋታና የከንፈር ወዳጅ መመሰረቻ ቀን ነው፣ ከነሃሴ አስራ ስድስት እስከ ሰላሳ የልጃገረዶች የነፃነት ቀን ሲሆን እንግጫ፣ እንቁጣጣሽ አበባ ያለበት ቦታ የሚለዩበት፣ ቅድመ ዝግጅት የሚያደርጉበት ከጳጉሜ አንድ እስከ አምስት ወይም ስድስት ወንዝ የሚጠመቁበትና እንግጫ እየነቀሉ የሚሰበስቡበት ቀን ነው፡፡ ጳጉሜ 5 ወይም 6 ደግሞ ማታ ወንዶች ችቦ ሲያበሩላቸው እንግጫውን ከእንቁጣጣሽ አበባው ጋር የሚጎነጉኑበት እለት ነው፡፡ መስከረም አንድ ደግሞ ጥዋት በመነሳት እንግጫውን በአንገታቸውና በእራሳቸው አስረው በቤትና በቤተክርስትያን እየዞሩ የተጎነጎነውን እንግጫ የሚያስሩበት እንዲሁም በአካባቢያቸው ካሉት ጎረምሶች ጋር በነፃነት ሲጫወቱ የሚውሉበት፣ እንዲሁም አጠቃላይ የማህበረሰቡ አባላት አሮጌው ዓመት ማለቁን አዲሱ ዓመት መግባቱን አስመልክቶ በደስታ በዓሉ የሚያከብርበት ስርዓተ ክዋኔ ያካሂዳሉ፡

ሁለተኛው የክዋኔው ማህበረ ስነልቦዊ ፋይዳ መተንተን የሚል ነው፡፡ በዚህ ጥናት የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ በእንግጫ ነቀላ ስርዓቱ የከንፈር ወዳጅ መመሰረቻ፤ የነበረውን ወዳጅነት ማስቀጠያ የመሰሉ ማህበራዊ ትስስር እንደሚፈጥሩና ከአሮጌው ዓመት ወደ አዲሱ ዓመት በሰላም መሸጋገርን ማብሰርና ከአካላዊና መንፈሳዊ ደዌ መንፃትን የመሰሉ ስነልቦናዊ እርካታ እንደሚያገኝ ከጥናቱ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
ጥናቱ ከግብ ያደረሰው የመጨረሻው ንዑስ ዓላማ የክዋኔውን ትዕምርት መተርጎም ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከወኑ የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ከዋኔዎች ላይ የሚሳተፉት ልጃገርዶች የርግቧ ተምሳሌት፣ ርጥቡ ሳር ርግቧ የጥፋት ውሃው መጉደሉን ለመግለፅ የምስራች ያመጣችው፣ የሳሩ አለመዘርዘር የኖህን ንፅህና የወከሉ ሲሆን የእንቁጣጣሽ አበባው ስጦታ ደግሞ ጠቢቡ ሰሎሞን ለማክዳ (ለንግስተ ሳባ) ለአዲስ ዓመት የሰጣትን ስጦታ ተምሳሌት ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ስርዓተ ክዋኔው፣ በክዋኔው የሚሳተፉ አካላትና የሚጠቀሙባቸው ቁሶች ትዕምርት የማህበረሰቡ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ዳራዎችን የወከሉ ናቸው፡፡

### 5.2. የይሁንታ ሃሳብ

በዚህ ጥናት ከተገኙ ግኝቶች በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ተቀምጠዋል፡
፡

- ✓ የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የማህበረሰቡን የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ስርዓተ ክዋኔ በተፈጥሯዊ መቼቱ በተገቢው መንገድ በየዓመቱ እያስጠና በነበረው ባህላዊ እሳቤና እሴት እንዲቀጥል ቢያደርግ፡፡

- ✓ በባህል ጥናት ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ምሁራን በታዋቂ መጣጥፎች (ጆርናሎች) ላይ በማሳተም ለሌላው ማህበረሰብ የማህበረሰቡን የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ከዋኔ ለማስተዋወቅ የራሳቸውን አስተዋፅኦ ማብርከት ቢችሉ፡፡
- ✓ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የማህበረሰቡን ማህበረ ስነልቦናዊና ትዕምርታዊ ጉዳዮች መግለጫ የሆነውን የእንግጫ ነቀላ ስርዓተ ክዋኔ በልማት ስራቸው አካተው በየዓመቱ ማህበራዊ እሴቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከበር በማድረግ በባህሉ የሚኮራ ትውልድ ማፍራት የሚቻልበትን መንገድ ቢያመቻቹ፡፡
- ✓ የማህበረሰቡ መገለጫ የሆነው የእንግጫ ነቀላ ክብረ በዓል ይዘቱንና ስርዓተ ክዋኔውን በጠበቀ መልኩ እንዲቀጥል የማህበረሰቡ የእድሜ ባለፀጋና የሀይማኖት አባቶች በሚገናኙበት ማህበራዊ ተቋማት ሁሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት ቢያካሄዱ፡፡

## 6. ዋቢ ጽሁፎች


Bell, C. (1977). *Ritual, perspectives and dimensions.* Oxford University press. https://voidnetwork.gr/wp-content/uploads/2016/09/Ritual.-Perspectives-and-Dimensions-by-Catherine-Bell.pdf

Cooke, B. & Macy, G. (2005). *Christian symbol and ritual: An introduction.* New York: Oxford University Press. https://www.semanticscholar.org/paper/Christian-symbol-and-ritual-%3A-an-introduction-Cooke-Macy/c09b7431210bd346ce53d2729851a9a05d34581e

Dorson, R. M. (1972). *Folklore and folk life: An introduction.* The university of Chicago press: London. https://www.scirp.org/reference/referencespapers?referenceid=243809

Eriksen, H. T. (2001). *Small places, large issues: An introduction to social and cultural anthropology.* 2nd Ed, London: Pluti Press. https://toleratedindividuality.wordpress.com/wp-content/uploads/2015/02/small-places-large-issues-an-introduction-to-social-and-cultural-anthropology-culture-and-society.pdf

Kyriakidis, E. (2007). *The archaeology of ritual.* Los Angeles: Cotsen Institute of Archaeology. https://escholarship.org/uc/item/2r21b9wc

Mcleod Julie and Rachel Thomson, (2010) *Researching Social Change.* Losangeles /London/New Delhi:SAGE Publication Ltd

Rappaport, A. (1992). *Ritual.* In Richard Bauman (Ed). Folklore, cultural

performance and popular entertainments. Communications Centered Hand Book. New York: Oxford University Press. PP 249-260. https://www.scribd.com/document/656555534/Richard-Bauman-Folklore-Cultural-Performances-Z-lib-org

Salamone, A., & Frank (eds.). (2004). *Encyclopedia of religious rites, rituals, and festivals.* ROUTLEDGE, New York: London. https://www.academia.edu/50736071/Encyclopedia_of_Religious_Rites_Rituals_and_Festivals

Sims, M., & Stephens, M. (2005). *Living folklore: An introduction to the study of people and their traditions.* Utah state university. https://www.perlego.com/book/2811157/living-folklore-introduction-to-the-study-of-people-and-their-traditions-pdf

Turner, V. (1969). *The ritual process: Structure and anti-structure*. New York: Aldina De Gruvter. https://monoskop.org/images/9/90/Turner_Victor_The_Ritual_Process_Structure_and_Anti-Structure.pdf

ጌታቸው እምሬና ሌሎች፡፡ (2011 ዓ.ም)፡፡ *የእንግጫ ነቀላ በዓል ታሪካዊ ዳራ፣ ክዋኔ፣ ፋይዳ፣ ተግዳሮቶችና ምቹ አጋጣሚዎች፡* የሃዲስ ዓለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ሰባተኛው አገር አቀፍ አውደ ጥናት መድብለ ጉባኤ፡፡